መጋቢት 2004 ዓ.ም.

# <u>አሳሳቢውን የትምህርት ስርዓት ዝቅጠት በኢሮብ ወረዳ ለመቅረፍ ምን መደረግ አለበት?</u>

**ክፍል አንድ፣**

## <u>መልስ የሚያስፈልጋቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች፣</u>

**ከበየነ ገብራይ፣ ደንማርክ**

በዚህ ርእስ ላይ ለመጻፍ መነሻ የሆነኝ በቅርብ ጊዜ የተቋቋመውና “Irob Scholarship and Education Support Program (ISESP)" በሚል ስም በራስ ተነሳሽነት የተመሰረተውን የበጎ አድራጎት ማኅበርን ከሚመሩት አንዱ የሆኑት አቶ ዚያደ ኃይሉ በጃንዋሪ 16 ቀን 2012 ዓ.ም.ፈ በጎሮን ፈይስቡክ ፎረም ላይ የለጠፉት ቀጥሎ የተቀመጠው አጭር የእንግሊዝኛ መልእክት ነው።

የአቶ ዚያደ ኃይሉ አጭር የእንግልዝኛ መልእክት እንደሚከተለው የሚል ነበር።

”(Living in Alitiena, thinking of Israel)
Analyze this: For starters here is the report card on Irob education according to the Woreda chief: out of 300 students who sat for 10th grade exams only 39 merely passed. And out of those 39 who participated in preparatory (12th) exams only 7 passed with no particular flying colors. And only God knows how those 7 succeed in completing the university degree. Besides school drop rate is hovering between 30%-50% - go fiqure out people…”

በርግጥ አቶ ዚያደና እሳቸውን መሰል ወገኖቻችን በራስ ተነሳሽነትና የበጎ አድራጎት ሀሳብ አፍላቂነት፣ በድህነት ምክንያት ከፍተኛ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ያልቻሉ 12 ተማሪዎችን ለ4 ዓመታት ለመርዳት ፕሮጀክት ቀርጸው መንቀሳቀሳቸውና አዎንታዊ ውጤት ማስመዝገባቸው ሁላችንም ሊያስደስት የሚገባ በጎ ተግባር ነው። እንዲሁም ISESP ላደረገው የእርዳታ ጥሪ በተለያየ ክፍላተ-ዓለማት የሚገኙ ኢሮቦች እያደረጉት ያለ የገንዘብ ማሰባሰብና የሰጡት አበረታች መልስም የሚያኮራና ለወደፊትም መበረታታት የሚኖርበት በጎ ተግባር ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሆኖ ግን ከላይ የተቀመጠው የአቶ ዚያደ አጭር መልእክትን ልብ ብለን ከተመለከትን፣ ዛሬ በኢሮብ ወረዳ ያለው የትምህርት አሰጣጥ ስርዓት ገና ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ከፍተኛ የሆነ ችግር ያለበት መሆኑን በግልጽ ለመገንዘብ ያስችናለል። በመሆኑም፤ እኔ ትምህርትን በተመለከተ በወረዳችን ዛሬ ያለው ችግር የተወሰኑ ተማሪዎች ችግርን በመፍታት ሊቀረፍ የሚችል አይደለም እላለሁ። ስለሆነም በኢሮብ ወረዳ ያለውን መሰረታዊ የትምህርት ስርዓት ያለበት ችግሮች ከስር መሰረቱ በሚገባ በባለሙያዎች ተገምግሞ፣ ባለድርሻዎችን ሁሉ ባካተተ መልኩ ጥልቅ ውይይት ተደርጎበት አጠቃላይ መፍትሄ ፍለጋ ላይ መተኮር አለበት እላለሁ። ለዚህም፣ አሁን ያሉንን የተለያዩ የመወያያ መድረኮች በመጠቀም፣ በአካል ልንገናኝ የምንችልም በአካል በመገናኘት በዚህ ጉዳይ ላይ ጥልቅ ውይይት ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

ዛሬ በኢሮብ ወረዳ የሚኖሩ ወጣቶቻችን አስተሳሰብ፣ ተማሪዎች በትምህርት ላይ ያላቸው ተሳትፎና ውጤት አመላካች የሆነው አጭር የአቶ ዚያደ ኃይሉን መልእክት ልብ ብሎ ለተመለከተ የኢሮብ ብሂረሰብ ተወላጅ እጅግ አስደንጋጭና አሳሳቢ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። የአቶ ዚያደ መልእክት ገና ከጅምሩ የሰጡትን ርእስ በማየት በቀላሉ የሚገባህ ሆኖ በርካታ ጥያቄዎችን እንድናነሳ የሚያስገድደን ሆኖ ይገኛል። ስለሆነም ለዛሬው ሁላችን በየግላችን ልናብላላቸውና መልስ

ልንፈልግላቸው የሚገቡን ናቸው የሚላቸውን ነጥቦች ከአቶ ዚያደ ኃይሉ አጭር መልእክት እየጠቀስኩ ለውይይታችን መንደርደሪያ ሊሆኑ ይችላሉ ብዬ የገመትኩዋቸውን ጥያቄዎች ለማስቀመጥ እሞክራለሁ።

"Living in Alitiena, thinking of Israel"

1. ወጣቶቻችን በአካል በዓሊተና እየኖሩ ለምንድነው ስለ እስራኤል(ባእድ አገር) የሚያማልሉት/የሚያስቡት?
2. ወጣቶቻችን በአካል ዓሊተና እየኖሩ ህልማቸው ስለ እስራኤል እንዲሆን ያስገደዳቸው ምክንያት ወይም የመንስኤ ሓሳብ ምንድን ነው?

"out of 300 students who sat for 10th grade exams only 39 merely passed."

1. ለ10ኛ ክፍል ፈተና 300 ተማሪዎች ተቀምጠው 39 ብቻ ፈተናውን አልፏል። የቀሪዎቹ 261 ተማሪዎች እጣ-ፈንታ ምንድነው?
2. የት ገቡ?
3. መጻኢ ዕድላቸውስ ምን ሊሆን ይችላል?
4. ከ300 ተማሪ 261 ፈተናውን ለማለፍ አለመቻል ምክንያት ምን ይሆን? ምንስ ያመላክተናል?

"And out of those 39 who participated in preparatory (12th) exams only 7 passed with no particular flying colors"

39 ተማሪዎች ለ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ተቀምጠው ከ39ኙ 7 ብቻ ፈተናውን ማለፋቸው ተዘግቧል። ስለሆነም የ32ቱ እጣ-ፈንታ ከላይ ከተጠቀሱት 261ዱ እጣ-ፈንታ ጋር ተመሳሳይነት አለው። በመሆኑም ከ300 ተማሪዎች ውስጥ 7 የ12ኛ ክፍል መልቀቅያ ፈተና አልፈው ከፍተኛ ትምህር የመከታተል እድል ገጥሞዋቸዋል። 293ት ወጣቶች ምን ይሆናሉ?

"Besides school drop rate is hovering between 30%-50% - go fiqure out people..."

ከ30 እስከ 50% የሚሆኑ ተማሪዎች ዓመታዊ ትምህርታቸውን ሳይፈጽሙ በማኽል ያቋርጣሉ ተብሎዋል።

1. ይህን ያህል ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ለምን ትምህርታቸውን በማኽል ያቋርጣሉ?
2. ችግራቸው ምንድን ነው? .......ወዘተ የሚሉና ሌሎች መሰል ጥያቄዎች ጥልቅ ውይየትና አስቸኳይ መፍትሂ የሚያስፈልጋቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች ናቸው። ስለሆነም በነዚህና ሌሎች መነሳት አለባቸው የምትሉዋቸው ጥያቄዎች፣ ወይም ሃሳቦች በማንሳት ሁላችሁም በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ በሚደረገው ውይይት እንድትሳተፉና መፍትሂ ሃሳቦች እንድታፈልቁ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

በክፍል ሁለት ለምን ወጣቶቻችን በአካል በዓሊተና እየኖሩ ስለ እስራኤል (ባእድ-አገር) ያልማሉ?

ለዚህ ለወጣቶቻችን በአካል በዓሊተና እየኖሩ ህልማቸው ስለ እስራኤል እንዲሆን ያስገደዳቸው ምክንያት ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመዳሰስ እሞክራለሁ።

መልካም ውይይት።